# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት

## የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር

**ሀገር አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና የሙያ ብቃት ምዘና፣ እውቅናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ የተሻሻለ መመሪያ ቁጥር 912/2014 አጭር ማብራሪያ**

ሰኔ 2014 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# ክፍል አንድ

## 1. ማብራሪያ

### 1.1. መግቢያ

የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባርን ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 1097/2011 አንቀፅ 26 ለሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚንስቴሩ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሰረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀጽ 10 (3) እንዲሁም አንቀጽ 14 (1) እና (2) ለማስፈጸም አገር አቀፍ ሙያ ብቃት ምዘና፣ እውቅናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ አገር አቀፍ ሙያ ብቃት ምዘና፣ እውቅናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር አጽድቆ አዋጁን ሲያስፈጽም ቆይቶአል ፡፡ በተሸሻለው የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1263/2014 መሠረት ከተቋቋሙት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች አንዱ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር ሲሆን ለሚኒስቴሩ በተሰጠው ስልጣንና ተግባር ማእቀፍ ውስጥ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አዋጅ ቁጥር 954/2008 እንደሚያስፈጽም በግልጽ ያማመላክታል፡፡

በዚህ መሰረት የስራና ክህሎት ሚኒስቴር በሁሉም ደረጃ ተቀባይነት ያለው ውጤትን መሰረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራምበጥራና በብዛት በማሰልጠን ፤ እንዲሁም በልምድ በተገኘ ዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት እውቅና የሚሰጥ ስርአት በመዘርጋት፤ የሙያ ብቃትን በምዘና በማረጋገጥ ዕውቅና እና የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት መስጠት የሚያስችል አሰራር አጠናክሮ መቀጠል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የምዘና ስርዓቱን አግባብነት፣ ጥራት ፣ተደራሽነትና ፍህታዊነት ለማረጋገጥ እንዲያስችል በሀገር አቀፍ ደረጃ በተጠናው የትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ በተመላከተው ምክረ ሀሳብ መሰረት ደረጃ በደረጃ ይሰጥ የነበረው አገር አቀፍ የሙያ ብቃት ምዘና አሰልችና ሀብት አባካኝ እንድሁም ኢንዱስትሪዎችም ስልጠና አጠናቃቂዎችን በውጤታቸው አወዳድረው ለመቅጠር ያልተመቸና ውድድርን የሚያበረታታ ሆኖ ባለመገኘቱ የደረጃ ደረጃ ሽግግር በማሰልጠኛ ተቋም የውስጥ ምዘና ማስተግበሪያ መመሪያ ቁጥር 883/2014 እንድሸፈን በመደረጉ፤ ሰልጣኞች ወደ ስራ አለም /World of work/ ለመሰማራ ሲዘጋጁ ብቻ ሀገር አቀፍ የብቃት ምዘና መሰጠቱ የስልጠና ጥራትና አግባብነት ዙሪያ ከፍተኛ ለውጥ እንደሚያመጣ በተለያዩ ጥናቶችና የውይይት መድረኮች አረጋግጠዋል፡፡

በመሆኑም  አገር አቀፍ ሙ.ያ ብቃት ምዘና፣ እውቅናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሰልጣኞች በሚያጠናቅቁበት ደረጃ እንዲመዘኑ ማድረግ በነባሩ መመሪያ ያጋጥሙ የነበሩ ችግሮችን  በመፍታ እና ከተቋም ውስጥ ምዘና ማስተግበሪያ መመሪያ ጋር  ማጣጣም ወሳኝ በመሆኑ እንድሁም ከአሁን በፊት የነበረው አገር አቀፍ የሙ.ያ ብቃት ምዘና፣ እውቅናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ  መመሪያ የመዛኞችንና የሱፐርቫይዘሮችን ተጠያቂነት ያላካተተ በመሆኑ መመሪያውን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## 1.2. የመመሪያው መሻሻል አስፈላጊነት፤

- ከትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ ጥናት ምክረ ሀሳብ መሰረት ደረጃ በደረጃ ምዘና ቀርቶ በስልጠና ማጠናቀቂያ መውጫ አገር አቀፍ የሙ.ያ ብቃት ምዘና፣ እውቅናና የምስክር ወረቀት እንድሰጥ በማመላከቱ እና አሰፈላጊነቱም ስለታመነበት፡
- ነባሩ መመሪያ የሱፐር ቫይዘሮችንና የመዛኙን ተጠያቂነት በግልጽ ያላስቀመጠ ባለመሆኑ ፤ሱፐር ቫይዘሮችንና መዛኞች የጥቅም ግጭት ሲያጋጥም የሚፈታበት አግባብ በነባሩ መመሪያ ባመቀመጡ በምዘና ስርአቱ ላይ ታማኝነት አሳጥቶት በመቆየቱ፤
- የሚዘጋጀው የምዘና ጥያቄ ብዛት አይነት  በግልጽ በነባሩ መመሪያ ላይ ባመመላከቱ በምዘና ጥራቱ ላይ አሉታዊ ጎን በማሳደሩ በዚህ መመሪያ ይህንንም ችግር መፍታት አስፈላጊ በመሆኑ፤
- በቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርትና ስልጠና አዋጅ ቁጥር 954/2008 አንቀጽ12 (1) መሰረት ሚኒስቴሩ የሙ.ያ ብቃት ምዘና ተመዛኞች በሚመዘኑበት የሙ.ያ ዘርፍ የሚፈለገው ብቃት ያላቸው ስለመሆናቸው ለመወሰን በሚኒስቴሩ በተዘጋጀ  መመሪያ መሰረት እንደሚከናወን በመደንገጉ ፤
- ረቂቅ ሀገር አቀፍ የቴክኒክና ሙ.ያ ስልጠና የሙ.ያ ብቃት ምዘና፣ እውቅናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ  መመሪያ የቴክኒክና ሙ.ያ ስልጠና ማሰልጠኛ ተቋም የውስጥ ምዘና ማስተግበሪያ መመሪያ ቁጥር 883/2014 ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ሁኖ ስለተገኘ መመሪያው ሊሻሻል ችሏል፡፡

## 1.3.የረቂቅ መመሪያው አላማ

በስራና ክህሎት ሚኒስቴር የቴክኒክና ሙ.ያ ስልጠና የለውጥ ሀሳብ መሰረት ብሄራዊ የደረጃ በደረጃ ምዘና በተቋም ውስጥ በመስጠት  ወጪ እና ጊዜን ቆጣቢ፤ የተመዛኞችን ብቃት መለካት የሚያስችል  ሀገራዊ የብቃት ምዘና ስርአት በመዘርጋት በሙያው የሚተማመን ስራ ፈጣ  የሰው ኃይል በማፍራት  ለኢንዱስትሪው ማቅረብ ነው፡፡

## 1.4.የዋና ዋናዎቹ አንቀጾች  ዝርዝር ማብራሪያ፤

የተሻሻለው ረቂቅ መመሪያ መግቢያ መመሪያውን ለማሻሻል ያሉትን ችግሮች አይቶ አስፈላጊነቱን የሚገልፅ ሲሆን ከዚህ በፊት የነበሩ ችግሮችን እና ይህ መመሪያ ለማሻሻል የህግ ምንጭ የሆነውን ስልጣን ጠቅሶ አስቀምጧል፡፡

የተሻሻለው ረቂቅ መመሪያ ክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን ያካተተ ሲሆን በአንቀጽ 1 ስለ መመሪያው አጭር ርዕስ የሚጠቅስ ሆኖ ይህ መመሪያ «በቴክኒክና ሙያ ስልጠና የአገር አቀፍ ሙያ ብቃት ምዘና፣ እውቅና እና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ የተሻሻለ መመሪያ፡፡» ተብሎ የተጠቀሰ መሆኑን አስቀምጧል፡፡

የተሻሻለው ረቂቅ መመሪያ አንቀጽ 2 ስር  በመመሪያው በተደጋጋሚ የተጠቀሱ ቃላትና ሐረጎችን ትርጓሜ የሚገልጽ ሲሆን በተለይም መመሪያው መሰረት የሚያደርገው በሁሉም ደረጃ ተቀባይነት ያለው ውጤትን መሰረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ስርዓት በመደበኛና መደበኛ ባልሆነ ፕሮግራም እንዲሁም በልምድ በተገኘ ዕውቀት፣ ክህሎት እና የስራ ተነሳሽነት ብቃትን በሙያ ብቃት  ምዘና በማረጋገጥ ዕውቅና እና የብቃት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት  መስጠት መሆኑን ይጠቅሳል። በተሻሻለው ረቂቅ መመሪያው አንቀጽ 3 ላይ የተጠቀሰው ስለተሻሻለው የሙያ ብቃት ምዘና መመሪያ አላማውን በግልጽ አስቀምጦአል፡፡

በረቂቅ መመሪያው አንቀጽ  4 ላይ የተጠቀሰው ስለተፈጻሚነት ወሰን የሚገልጽ ሲሆን መመሪያው በሁሉም የመንግስት፤ የግል እና መንግስታዊ ያልሆኑ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና  ተቋማት፣ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ ኤጀንሲዎች/ማዕከላት/ባለስልጣን፣ ምዘና ማዕከላት፣ በመዛኞች እና በተመዛኞች እንዲሁም መመሪያውን በሚያስፈጽሙና በሚፈፅሙ አካላት  ሁሉ ተፈፃሚነት እንደሚኖረው ይደነግጋል፡፡ ለዚህ የተፈጻሚነት ወሰን መነሻ የሆነው የህግ መሰረት አዋጅ ቁጥር 954/2008 ሲሆን  በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ (3) ሚኒስቴሩ ከክልል አግባብነት ካለው አካል ጋር በመመካከር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለሙያ ብቃት ምዘና ማእከላት እውቅና ይሰጣል ይላል፡፡ እንድሁም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 14 ንኡስ አንቀጽ (1)  በሙያ ምዘና መሰረት ብቃቱን ያረጋገጠ ማንኛውም ሙያተኛ በኤጀንሲው ስም በብቃት ማእከላት በኩል የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል በማለት ተደንግጎአል፡፡ ይህ ማለት የሙያ ብቃት ምዘና እና የምስክር ወረቀት በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ በሆነ መልኩ እንደሚዘጋጅ በማያሻማ መልኩ መደንገጉን ያሳያል፡፤በመሆኑም በክልል ደረጃ ከተቋቋሙት አግባብ ካላቸው አካላት

ጋር ምክክር ተደርጎበት የተዘጋጀ ከመሆኑም ባሻገር በነባሩም መመሪያ ሲሰራበት የቆየና ልምምድ ያለ በመሆኑ የተፈጻሚነት ወሰኑ በሀገራችን በሚቋቋሙ በመንግስት፤ በግልና መንግስታዊ ባልሆኑ ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡

የተሻሻለው ረቂቅ መመሪያ ክፍል ሁለት አንቀጽ 5 ስለ አገር አቀፍ የሙያ ብቃት ምዘና እና እውቅና አሰጣጥ በመጥቀስ ንኡስ አንቀጽ 5.1 በተዘረዘሩት ንኡስ አንቀጾች ላይ ስለአገር አቀፍ የሙያ ብቃት ምዘና መሳሪያዎች ዝግጅት ሂደት በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ እንዲሁም በንዑስ አንቀጽ 5.2.1 ስር በተዘረዘሩት ንኡስ አንቀጾች ላይ የሙያ ብቃት ምዘናን ለማከናወን የሚያስፈልጉ መስፈርቶች፣በንዑስ አንቀጽ 5.2.2 በተዘረዘሩት ንኡስ አንቀጾች ላይ ስለምዘና የድርጊት መርሀ-ግብርና የክፍያ ስርዓት 5.2.3 በተዘረዘሩት ንኡስ አንቀጾች ላይ ስለሙያ ብቃት ምዘና ሂደት በንዑስ አንቀጽ 5.2.4.1 የምዘና ማእከል ዕውቅና አሰጣጥ ስርዓት በማስቀመጥ በ5.2.4.2 ላይ የምዘና ማዕከል እውቅና አሰጣጥ መስፈርቶች በ5.2.4.2 ላይ የመዛኝ እውቅና አሰጣጥ በሚል በዝርዝር ተቀምጧል፡፡

የተሻሻለው ረቂቅ መመሪያ ክፍል ሶስት አንቀጽ 6 የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ብሄራዊ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና መስፈርቶችን በዝርዝር በማስቀመጥ አብራርቷል፡፡ ንዑስ አንቀጽ 7 የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት አንቀጽ 8 ምትክ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፤ አንቀጽ 9 የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ትክክለኛነት ስለማረጋገጥ ሂደት በዝርዝር ያስረዳል፡፡

የተሻሻለው ረቂቅ መመሪያ ክፍል አራት አንቀጽ 10 የቴክኒክና ሙያ ስልጠና አስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት ከፌደራል እስከ ከተማ ድረስ ያለውን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ክፍል አምስት አንቀጽ 11 የሱፐርቫይዘር፤ መዛኝ እና ተመኛኝ መብትና ግዴታዎችን በዝርዘር አስቀምጦአል፡፡ አንቀጽ 12 የዲሲፕሊን እርምጃ አፈጻጸም እና አንቀጽ 13 የቅሬታ አቀራረብ ስርዓት፤ ክፍል ስድስት አንቀጽ 14 የመሸጋገሪያና ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች እና መመሪያ የሚጸናበትን ጊዜ አስቀምጧል፡፡

## ክፍል ሁለት

2. **የመመሪያው አዘጋጅ ኮሚቴ አዘገጃጀት፤ የዝግጅት ሂደትና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፤**

**2.1.የረቂቅ መመሪያው አዘጋጅ ኮሚቴ አባላት አደረጃት፤**

ቀደም ሲል ስራውን ይመራ የነበረው የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ማኔጅመንት ኮሚቴ ከፍኖተ ካርታው ጥናት እንድሁም በየወቅቱ ከክልሎች ጋር በሚካሄድ ጉባኤ ላይ በሚነሱ ውይይቶች በመነሳት መመሪያ ላይ መሻሻያ ረቂቅ የሚያቀርብ ኮሚቴ እንድደራጅ ተደርጎአል፡፡ የኮሚቴ አባላትም ከኤጀንሲው ማኔጅመንት ኮሚቴ አባላት መካከል ልምድ ያላቸው ሁለት የመካለኛ ደረጃ አመራሮች ከኤክስፐርር ሁለት እንድሁም ከክልል ሦስት በድምሩ ሰባት አባላት ያሉት ኮሚቴ እንድዋቀር ተደርጎ ረቂቅ መመሪያውን በ15 ቀን ውስጥ ሰርተው እንዳቀርቡ ጊዜ ተሰጥቶአቸው በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ የመመሪያውን ማሻሻያ ሰርተው አቅርበዋል፡፡

**2.2.2 በረቂቅ መመሪው ላይ የተካሄ ውይይትና ተሳተፊ ባለድርሻ አካት፤**

- በመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ መመሪያው ላይ የ11 የክልል የሙያ ብቃት ማእከል ኤጀንሲዎች ከፍተኛ ባለሙያዎች እን ከፌደራል መስሪያቤቶች 13 ባለሙያዎች በአዳማ ከተማ በተዘጋጀ የ2 ቀን ወርክ ሾፕ ላይ በማሳተፍ ግባት የማሰባሰብ ስራ ተከናውኖአል፡

- በአዳማ ውርክሾፕ የተገኘውን ግባት በማካተት ሰነዱን በማሻሻል ለ11ዱም ክልሎች በደብዳቤ ረቂቅ መመሪያውን በመላክ በ20 ቀን ውስጥ በክልል ደረጃ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት አወያይተው አስተያየታቸውን እንድልኩ በተላከላቸው መሰረት አንድ ወር ወስደው የሚመለከታቸውን አካላት አወያይተው በጽሁፍ ገንቢ አስተያየታቸውን 9 ክልሎች ልከዋል፡፡

- የመመሪያ አርቃቂ ኮሚቴው ከክልል የተላከውን ግብአት አዳማ ከተማ ለ3 ቀን ገምግሞ ጠቃሚ የሆኑትን ሀሳቦች በማካተት መመሪያውን የማበልጸግ ስራ አከናውኖአል፡

- ኮሚቴው የክልሎችን አስተያየት ካካተተ በኃላ ለኤጀንሲው ማኔጅመንት ኮሚቴ በማቅረብ ውይይት እንድካሄድበት ተደርጎ ተጨማሪ ግባት ከማኔጅመንት ኮሚቴው

ከተሰጠ በኃላ የክልል ቴክኒክና ሙ.ያ ቢሮ እና የሙ.ያ ብቃት ማረጋገጫ ኤጀንሲ ኃላፊዎች እና ከኢንዱስትሪዋች እና ከመዛኞች ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ተጠርተው አስተያየት እንድሰጡበት አቅጣጫ ተቀምጦአል፡

- በማኔጅመንት ኮሚቴው በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት የክልል ኃላፊዎች እና ከኢንዱስትሪዎችና ከመዛኞች በድምሩ 48 ኃላፊዎችና ባለሙዎች ተጠርተው የ8 ክልል ቢሮ ኃላፊዎችና የ11 ክልል የሙ.ያ ብቃት ማረጋገጫ ኤጀንሲ ኃላፊዎች እንድሁም የኢንዱስትሪዎች 13 ባለሙያዎች በተገኙበት ለ2 ቀን በአዳማ ከተማ ውይይት ተደርጎበት በጣም ጠቃሚ ግባት ተገኝቶበታል፡፡
- የመመሪያው አርቃቂ ኮሚቴው ከወርክሾፑ የተገኘውን ግባት በማካተት ለመጨረሻ ጊዜ ለኤጀንሲው ማኔጅመንት ኮሚቴ ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተደርጎበት ጠቃሚ ነጥቦች እንድካተቱ በማድርግ መመሪያው ለሚመለከተው አካል እንድላካ ተወስኖ ነበር፡፡ይህ በእንድህ እንዳለ
- ኤጀንሲው ፈርሶ የኤጀንሲው ስልጣንና ተግባር ለስራና ክህሎት ሚኒስቴር በመተላለፉ ረቂቅ መመሪያው ለስራና ክህሎት ሚኒስቴር ክቡራን ሚኒስቴሮች ቀርቦ በዝርዝር ከታየ በኃላ ሚኒስቴሮችም የሰጡትን ግባት የማካተት ለመጨረሻ አስተያየት ለኢፍዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር እንድላክ ተወስኖአል፡፡

## 2.3.በተካሄዱ ወርክሾፖችና የጽሁፍ አስተያየቶች ለመመሪያው መሻሻል በግባትነት የተወሰዱ ነጥቦች፤

- የደረጃ በደረጃ የሙ.ያ ብቃት ምዘና በተቋማት ውስጥ የሚሰጥ ሆኖ አገር አቀፍ የሙ.ያ ብቃት ምዘና ግን ሰልጣኙ በሚያጠናቅቅበት ደረጃ ሆኖ ነገር ግን ከሚያጠናቅቅበት ደረጃ ጀምሮ ወደታች ያሉትን ደረጃዎች ባካተተ መልኩ መመዘን እንዳለበት፣
- የንድፈ ሀሳብ ምዘናው ከደረጃ III የሚጀምር ሆኖ የተግባር ምዘናንም በማጠቃለል የደረጃ አንድና ሁለት በንድፈ ሀሳብ ጥያቄው ውስጥ የሚካተት ይሆናል፣ የንድፈ ሀሳብ ምዘና ጥያቄዎች ብዛትም 50 ሆኖ የጥያቄዎቹ ዓይነትም ምርጫ ብቻ መሆን እንዳለበት፣
- ደረጃ አራት እና አምስት የሚዘጋጁ ምዘና መሳሪያዎች የተግባርና የንድፈ ሃሳብ ምዘና የሚያካቱ ሆነው የንድፈ ሃሳብ ምዘናው ለደራጃ አራት 80 ለደረጃ አምስት 100 ጥያቄዎችን የሚይዝ እንዲሆን እና የጥያቄውም አይነት ምርጫ ብቻ መሆን

እንዳለበት፣

- አንድ ተመዛኝ በንድፈ ሀሳብ ምዘና ብቁ ለመሆን ቢያንስ 55% እና ከዛ በላይ ማስመዝገብ እንደሚኖርበት እንዲሁም የተግባር ምዘናውን ግን የቀረበውን ፕሮጀክት በሚፈለገው ደረጃና በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ሙሉ በሙሉ (100%) ማከናወን እንዳለበት፣
- ከደረጃ III እስከ V ያሉ የምዘና መሳሪያዎች (packages) የተግባር እና የንድፈ ሀሳብ ምዘና ጥያቄዎችን የሚያጠቃልሉ ሁነው፣ የጥያቄዎቹ ዓይነትም ምርጫ ብቻ መሆን መሆን እንዳለበት፣
- አገር አቀፍ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በፌደራል ስራና ክህሎት ሚኒስቴር በኩል እየታተመ ለክልል የሙያ ብቃት ስራን እንዲሰሩ በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ውክልና በመስጠት አገር አቀፍ ምዘና ወስደው ብቁ ለሆኑ ተመዛኞች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እንዲሰጡ መደረጉ መቀጠል እንዳለበት፣
- ስልጠናቸውን በደረጃ አጠናቀው ወደ ስራ ገበያው የሚቀላቀሉ መደበኛ ሰልጣኞችና የኢንዱስትሪ ተመዛኞች አገር አቀፍ የብቃት ምዘናውን በሚወስዱበት ደረጃ ብቃታቸው በምዘና ሲረጋገጥ ከታች ያሉ ደረጃዎችንና የሙያ ስያሜን የሚገልፅ የአገር አቀፍ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰጠት እንዳለበት፣
- የመውጫ ምዘናውን ተመዝኖ ኢንዱስትሪውን የተቀላቀለና ተመልሶ ስልጠናውን የሚቀጥል ባለሙያ ስልጠና አጠናቆ የሙያ ብቃቱን ያረጋገጠበትን ደረጃ ብቻ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት እንደሚኖርበት፣
- በተቋም ውስጥ ደረጃ በደረጃ ብቃታቸው በምዘና ያረጋገጡበት ደረጃና የብቃት አሃዶች ዝርዝር ከአገር አቀፍ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ጋር አባሪ ተደርጎ መሰጠት እንዳለበት፣
- የቴክኒክና ሙያ ስልጠና አጠናቃቂዎችን ቀጣሪ ኢንዱስትሪዎች የሰልጣኞችን የተቋማት የውስጥ ምዘና ሰርትፍኬት ውጤትና የብሄራዊ ብቃት ምዘና ሰርትፍኬት ዋጋ መስጠት እንደሚኖርባቸው ሀሳብ ተነስቷል፡፡
- የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀት እንዲሰጡ በህግ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት ብቁ ለሆኑ ተመዛኞች ያሰራጪቸውን የሙያ ብቃት የምስክር ወረቀቶች መረጃ ለፌደራል ስራና ክህሎት ሚኒስቴር በየሶስት ወር(3) ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው፣
- ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ አዲስ ተመዝጋቢዎች ላይ የደረጃ ደረጃ ሽግግር ምዘና የሚካሄደው በተቋማት ብቻ መሆን እንደሚኖርበት፣

- ተገቢ የሆነ ማሻሸያ ካልተደረገባቸው በስቀር ተመሳሳይ የምዘና መሳሪያዎችን በተከታታይ ለምዘና መጠቀም እንደማያሰፈልግ፣
- ማንኛውም በስልጠና ተቋማት የተገኘ የደረጃ በደረጃ ሽግግርም ሆነ የስልጠና ማጠናቀቂያ ሰርትፍኬቶች ተቀባይነት የሚኖራቸው ስልጠና አጠናቃቂው ሰልጣኝ በአገር አቀፍ ሙያ ብቃት ማረጋገጫ አካል አማካኝነት ተመዝኖ ብቃቱ ሲረጋገጥ ብቻ መሆን እንዳለበት፣
- አንድ መዛኝ በአንድ የሙያ ብቃት ምዘና ክፍለ-ጊዜ ለደረጃ ምዘና መመዘን የሚችለው ቢበዛ 15 ተመዛኞችን ብቻ መሆን እንዳለበት፡
- መዛኙ 5 ተመዛኞች ብቻ ለምዘና ከቀረቡ ያለምንም ተጨማሪ ክፍያ የመመዘን ግዴታ እንዳለበት፡፡
- የተመዛኞች ቁጥር ከ5 በታች ከሆነ የቀሪ ተመዛኞችን ክፍያ በመሸፈን መመዘን እንደሚችል በመመሪያው ላይ እንድመላከት፤
- በምዘና ወቅት ሁለትና ከዚያ በላይ መዛኞችን መጠቀም እንደሚኖርበት፣

በአገር አቀፍ ደረጃ በተጠናው የትምህርትና ስልጠና ፍኖተ ካርታ ጥናት ምክረ ሀሳብ እና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ሚኒስቴር የለውጥ ሀሳብ መሰረት አገር አቀፍ የሙያ ብቃት ምዘና፣ እውቅናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያን ለማሻሻል ከክልል እና ከፌደራል እንዲሁም ከኢንዱስትሪዎች የተወጣጣ አመራርና ባለሙያ ሀሳብ እንዲሰጥ ተደርጎ ከላይ የተዘረዘሩት ሀሳቦች ተሰብስበው ለመመሪያ ማሻሻያነት በግብዓትነት ተወስዷል፡፡